# ለግምገማ ወይም ለድጋሚ ግምገማ በቅድሚያ የተጻፈ ማስታወቂያ እና የስምምነት ጥያቄ

ለ ______________________________ ቀን ______________________________
(ወላጅ/ህጋዊ የሆነ ትምህርታዊ ውሳኔ ሰጪ)

አድራሻ ______________________________

በ ____________________ ፈንታ
(የተማሪ ስም)

______________________________

የልጅዎን የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ ለማስገባት [LEA] የሚከተለውን ስራ እንዲያጠናቅቅ ተጠይቋል ወይም ሐሳብ አቅርቧል። እባክዎ ምልክት የተደረገባቸውን ነገሮች ይከልሱ። ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ከ[LEA] ከትምህርት ሰራተኞች ጋር ለመወያየት ነፃነት ይሰማዎ።

## ሀ. የልዩ ትምህርት እርምጃ ቀርቧል፡ -

☐ **1. የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ለማካሄድ [LEA] ሀሳብ አቅርቧል ። (የወላጅ ፈቃድ ይፈለጋል)**

አሁን ባለው መረጃ ግምገማ ላይ በመመስረት (አስፈላጊ ከሆነ) የ IEP ቡድን (ወላጆችን ጨምሮ) የልጅዎን የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ለማካሄድ ሀሳብ ያቀርባል-የሚከተሉትን ውሳኔ ለማድረግ ቡድኑን በቀጥታ የሚረዳ አግባብነት ያለው መረጃ በሚቀጥለው ገጽ ላይ በተመለከቱት በታዎች ላይ ይሰበሰባል፡-

- ልጅዎ የተለየ ተሰጥኦ እና የትምህርት ፍላጎቶች ያለው ልጅ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን፣
- አሁን ያለው የትምህርት ስኬት ደረጃዎች እና ተዛማጅ የልጅዎ የእድገት ፍላጎቶች ለመወሰን፤ እና
- ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ይፈልግ እንደሆነ ለመወሰን ።

☐ **ምንም ተጨማሪ መረጃ አያስፈልግም። አሁን** ባለው የመረጃ ግምገማ ላይ በመመርኮዝ፣ ከላይ እንደተገለፀው የመጀመሪያውን ደረጃ ግምገማ ለማካሄድ ምንም ተጨማሪ መረጃ እንደማያስፈልግ ተወስኗል። ከዚህ በታች በተመለከቱት የልጅዎን የትምህርት ፍላጎቶች ለመወሰን ቡድኑን በቀጥታ የሚረዳ አስፈላጊ መረጃን የሚያቀርብ ነባር መረጃ ጥቅም ላይ ይውላል ።

ሆኖም ግምገማው እንዲጠናቀቅ የመጠየቅ መብት አልዎት። እንደዚህ ዓይነት ግምገማ እንዲካሄድ ከፈለጉ እባክዎን ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የትምህርት ቤት ተወካይ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ያነጋግሩ ።

☐ **{2] ድጋሚ ግምገማ ለማድረግ [LEA] ሐሳብ አቅርቧል። (የወላጅ ፈቃድ ይፈለጋል)**

አሁን ባለው መረጃ ግምገማ ላይ በመመስረት (አስፈላጊ ከሆነ) የ IEP ቡድን (ወላጆችን ጨምሮ) የልጅዎን ግምገማ በድጋሜ ለማካሄድ ሀሳብ ያቀርባል የሚከተሉትን ውሳኔ ለማድረግ ቡድኑን በቀጥታ የሚረዳ አግባብነት ያለው መረጃ በሚቀጥለው ገጽ ላይ በተመለከቱት በታዎች ላይ ይሰበሰባል፡-

- ልጅዎ የተለየ ተሰጥኦ እና የትምህርት ፍላጎቶች ያለው ልጅ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን፤
- አሁን ያለው የትምህርት ስኬት ደረጃዎች እና ተዛማጅ የልጅዎ የእድገት ፍላጎቶች ለመወሰን፣
- ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በቀጣይነት መፈለጉን ለመወሰን፤ እና
- በልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ላይ ማናቸውንም ተጨማሪዎች ወይም ማሻሻያዎች ልጅዎ በልጅዎ IEP ውስጥ የተዘረዘሩትን የሚለካ ዓመታዊ ግቦች እንዲያሟላ እና እንደአስፈላጊነቱ በአጠቃላይ የሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲሳተፍ ለማስቻል አስፈላጊ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ።

☐ ምንም ተጨማሪ መረጃ አያስፈልግም። አሁን ባለው የመረጃ ግምገማ ላይ በመመርኮዝ፣ ከላይ እንደተገለፀው የመጀመሪያውን ደረጃ ግምገማ ለማካሄድ ምንም ተጨማሪ መረጃ እንደማያስፈልግ ተወስኗል። ከዚህ በታች በተመለከቱት የልጅዎን የትምህርት ፍላጎቶች ለመወሰን ቡድኑን በቀጥታ የሚረዳ አስፈላጊ መረጃን የሚያቀርብ ነባር መረጃ ጥቅም ላይ ይውላል ።

ሆኖም ግምገማው እንዲጠናቀቅ የመጠየቅ መብት አልዎት። እንደዚህ ዓይነት ግምገማ እንዲካሄድ ከፈለጉ እባክዎን ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የትምህርት ቤት ተወካይ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ያነጋግሩ ።

☐ 3. **የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ለማካሄድ [LEA] ፈቃደኛ አልሆነም ። (የወላጅ ፈቃድ አይፈለግም)**

☐ 4. **እንደገና ለመገምገም [LEA] ፈቃደኛ አልሆነም ። (የወላጅ ፈቃድ አይፈለግም)**

______________________________ በ ______________________________
(የትምህርት ቤት ተጠሪ ሰው) (ስልክ)

| አዲስ መረጃ | ነባር መረጃ | |
|---|---|---|
| ☐ | ☐ | **ጤና/የሞተር ችሎታ -**<br>አጠቃላይ እና ጥሩ የሞተር ክህሎቶችን መገምገም ፣ እና/ወይም የበሽታ ወይም የጉዳት ማስረጃን ሊያካትት ይችላል ። ግምገማ ግራ እና ቀኝን መለየት (laterality)፣ አቅጣጫ መለየትን (directionality)፤ ሚዛን የመጠበቅን (balance)፣ በእንቅስቃሴና በእጅ በመነካካት የመማር ክህሎቶች (kinesthetic skills)፣ በእጅ በመነካካት የመማር ክህሎቶች (tactile skills)፣ ወይም ከመራመድ ጋር የተገናኘ ወይንም የአቀማመጥ (ambulatory/postural) ችግሮች ሊያካትት ይችላል. |
| ☐ | ☐ | **ራእይ**<br>የቅርቡ እና የሩቅ ነጥብ የማየት ችሎታን፣ የዓይን ጡንቻ ቁጥጥርን ፣ ጥልቅ ግንዛቤን ፣ ቀለምን ያለመለየትን ችግር (color blindness) እና አቅጣጫ / የመንቀሳቀስ ችሎታዎችን መገምገምን ሊያካትት ይችላል። |
| ☐ | ☐ | **መስማት**<br>ለጠሩ ድምፆች እና ንግግር፣ የመካከለኛው ጆሮ ተግባር ፣ ማዕከላዊ የመስማት ችሎታ ሂደት ክህሎቶች እና የድምጽ ማጉያ አስፈላጊነትን/አጠቃቀምን መገምገም ሊያካትት ይችላል ። |
| ☐ | ☐ | **ማህበራዊ/ስሜታዊ ሁኔታ/የባህሪ ሁኔታ -**<br>ከልጁ ትምህርት፣ ከግለሰባዊ ግንኙነቶች፣ ስሜቶች እና/ወይም አካላዊ ምልክቶች ጋር በተያያዘ መልኩ የማህበራዊ/ስሜታዊ/የባህሪ እድገትን ግምገማ ሊያካትት ይችላል። ተገቢውን አዎንታዊ የባህሪ ድጋፎችን ለመወሰን ሊተገበር የሚችል የባህሪ ምዘና (assessment) ወይም ግምገማ (evaluation) ሊያካትት ይችላል። |
| ☐ | ☐ | **አጠቃላይ የግንዛቤ ችሎታ (General intelligence) –**<br>አጠቃላይ የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ችሎታዎችን ግምገማ የልጁን የትምህርት ደረጃ፣ ችግር መፍታት ክህሎቶች፣ የፅንሰ-ሃሳብ የመረዳት ደረጃ፣ የግንዛቤ ስልቶችን አጠቃቀም እና/ወይም የማመዛዘን እና/ወይም የማጠቃለል ችሎታን (ability to generalize) ሊያካትት ይችላል። |
| ☐ | ☐ | **የትምህርት አፈፃፀም –**<br>የትምህርት ወይም የቅድመ-ትምህርት ክህሎቶችን እና የውጤታማነት ደረጃዎችን ከአጠቃላይ ስርአተ ትምህርቱ ጋር በተገናኘ መልኩ እንደ የቃል ወይም የፅሁፍ አገላለጽን፣ የንባብ ክህሎትን ወይም የመረዳት ችሎታን፣ የሂሳብ ስሌትን ወይም ምክንያታዊነትን ሊያካትት ይችላል። ዓይነ ስውር ወይም ማየት ለተሳነው ልጅ የብሬይል ትምህርት አስፈላጊነት ሊገመገም ይችላል። |
| ☐ | ☐ | **የመግባባት ሁኔታ –**<br>የልጁን መረጃ የማስተላለፍ እና የመረዳት ችሎታን እና ማህበራዊ ፍላጎትን እንደ ገላጭ እና ተቀባይ ቋንቋ፣ ንግግሮች፣ ድምጽ፣ ቅልጥፍና ወይም አጋዥ ግንኙነት ያሉ ክህሎቶችን ሊያካትት ይችላል። መስማት ለተሳነው ወይም መስማት ከባድ ለሆነበት ልጅ የልጁን ቋንቋ እና መግባባት ከግምት ውስጥ ማስገባትን መገምገም ይቻላል ። |
| ☐ | ☐ | **የሽግግር ክህሎቶች –**<br>ከስልጠና ፣ ከትምህርት ፣ ከሥራ ቅጥር ፣ ከትምህርት ኮርሶች እና ተገቢ ሆኖ ከተገኘ ገለልተኛ ሆኖ የመኖር ክህሎቶች ጋር የተያያዙ ተገቢ የሽግግር ምዘናዎችን ሊያካትት ይችላል ። |
| ☐ | ☐ | **ሌላ ይግለጹ፡** |

**ለ. ድርጊቱ ለምን እንደታሰበ ወይም እንደተከለከለ ማብራሪያ፡-**

**ሐ. የታሰቡ አማራጮች እና አማራጮቹ ለምን ውድቅ እንደተደረጉ፡**

**መ. ለታቀደው ወይም ተቀባይነት ላጣው ድርጊት እንደ መሰረት ጥቅም ላይ የዋለው የውሂብ (ዳታ) መግለጫ፡-**
(እያንዳንዱን የግምገማ ሂደት፣ ምዘና፣ መዝገብ ወይም ሪፖርት ለታቀደው ወይም ውድቅ ለተደረገው እርምጃ መሰረት ሆኖ ያገለገለውን በማጠቃለል)

**ሠ. ከታቀደው ወይም ከተከለከለው ድርጊት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ከግምት ውስጥ የገቡ ሌሎች ምክንያቶች፡-**

**የወላጅን መብቶችን ለመጠበቅ የአሰራር ሂደት ከለላዎች**

ልዩ ትኩረቶችን የሚሹ ልጆች ትምህርትን በተመለከተ ሁለቱም የእስቴትና እና የፌደራላዊ ህጎች ብዙ የወላጅ መብቶችን ያካትታሉ። ትምህርት ቤቱ ልጅዎን በሚመለከት ሊወስዳቸው የሚፈልገውን የእርምጃ ማሳሰቢያ መቀበል እና የልጅዎ የትምህርት እቅድ ቡድን አካል መሆን የመብትዎ ምሳሌዎች ናቸው። መብቶችዎን ማወቅ እና እነዚያን መብቶች ለመጠቀም እድል እንዳሎት ለማረጋገጥ እነዚህ ህጎች ትምህርት ቤቱ የተወሰኑ ቅድመ ሂደቶችን እንዲከተል ያዝዛሉ። ትምህርት ቤቱ በትምህርት አመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ የወላጅ መብቶች ቅጂ እንዲሰጥዎ ያስፈልጋል። ለግምገማ የመጀመሪያ ማጠቀሻ ሲደረግ የርስዎን መብቶች ቅጂ ተቀብለዋል ። መብቶችዎን በሚመለከት ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ተጨማሪ የመብትዎን ቅጂ ማግኘት ከፈለጉ የትምህርት ቤቱን የልዩ ትምህርት ዘርፍ ዳይሬክተሩን ወይንም የልዩ ትምህርት ዘርፍ አስተባባሪውን ማነጋገር ይችላሉ እና እነሱን በጥንቃቄ ማንበብ አለቦት።

## ተጨማሪ መረጃ

በእነዚያ ሕጎች የተሰጣቸውን የልዩ እርዳታ የሚሹ ልጆችን ለማስተማርና እና የወላጅ መብቶች (የአሰራር ቅደም ተከተል ከለላዎችን) ለመረዳት የፌዴራላዊና እና የስቴት ህጎችን እንዲረዱ ለማገዝ የሚከተሉትን የሰው ሀብት ምንጮች ማናቸውም ሊያነጋግሩ ይችላሉ፡- የካንሳስ ስቴት የትምህርት ክፍል። 800-203-9462፣ ካንሳስ የአካል ጉዳተኛ መብቶች ማዕከል (DRC) (877) 776-1541፤ Families Together, Inc. 800-264-6343፤ እና አውታረ መረብ (Networking) ለማግኘት 785-233-8732።

**መላኪያ**

እኔ ፣ ______________________

☐በእጅ ተሰጥቶአል ፣

☐በፖስታ ተልኳል ፣

☐ ሌላ ______________
(ይግለጹ)

ይህ ማስታወቂያ ለ______________________ ______________________
(ስም) (ቀን)

**የልዩ ትምህርትን (special education) ለመተግበር የስምምነት ጥያቄ**

*(አስፈላጊ ከሆነ)*

በተያያዘው ማስታወቂያ ላይ እንደተመለከተው የልዩ ትምህርት ትግበራውን እንድናከናውን ፈቃድ እንድትሰጡን እንጠይቃለን። ከላይ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ያለን የትኛውም አለመግባባት በጋራ ስምምነት፣ በሽምግልና ወይም በፍትህ ሂደት ሊፈታ ይችላል። የአማላጅነት እና የፍትህ ሂደቶች ማብራሪያ በተጠየቀ ጊዜ ይሰጣል ። የታቀደው እርምጃ(ዎች) የእርስዎን የጽሑፍ ፈቃድ እንደተቀበሉ ወዲያውኑ ሊጀምር ይችላል ። ይህ የመጀመሪያ ግምገማ ከሆነ የእርስዎ ስምምነት በ60 የትምህርት ቀን የጊዜ ገደብ ይጀምራል፣ ልጅዎ ብቁ ከሆነ፣ በእርስዎ ፈቃድ የሚጠናቀቀው የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በIEP መሰረት ነው። ይህን ማስታወቂያ አስመልክቶ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት የሚከተለውን ትምህርት ቤት ተወካይ ማነጋገር ይችላሉ:

______________________________ በ ______________________________

(የትምህርት ቤት ተጠሪ ሰው) (ስልክ)

**በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ለተገለጹት የልዩ ትምህርት ተግባራት ፍቃደኛ መሆን ከፈለጉ ወይም ፈቃድዎን መስጠት ካልፈለጉ፣ እባክዎን ይህንን ቅጽ (ከታች) ፈርመው እና ቀን ጽፈው ከላይ ለተመለከተው የትምህርት ቤት ተወካይ ይመልሱት።**

*ስምምነት መስጠት*

☐ እኔ በዚህ *ማስታወቂያ ውስጥ ለተጠቀሰው ግምገማ ወይም የድጋሜ ግምገማ ለልጄ* ***ስምምነት እሰጣለሁ።***
*ይህ ስምምነት በፈቃደኝነት እንደሆነ እና በማንኛውም ጊዜ ሊሻር እንደሚችል ተረድቻለሁ፣ ነገር ግን ይህ መሻር ስምምነት ከተሰጠ በኋላ እና ስምምነት ከመሰረዙ በፊት የሚፈጸመውን አይከለክልም።*

*ስምምነት አለመስጠት*

☐ እኔ *በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ለተጠቀሰው ግምገማ ወይም የድጋሜ ግምገማ ለልጄ* ***ስምምነት አልሰጥም*** *።*

______________________________ ቀን ____________________

(የወላጅ/ህጋዊ የትምህርት ውሳኔ ሰጪ)

______________________________ ቀን ____________________

(የወላጅ/ህጋዊ የትምህርት ውሳኔ ሰጪ)